# Learning by Ear 2013

መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE TWENTY-THREE: ጥሩና መጥፎ ዜና

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Ludger Schadomsky**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: ምህረት IN SCHOOL**

- ዳንኤል (M, 16)
- ምህረት (F, 15)
- ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)
- ንጉሴ (M, 16)
- GROUP OF STUDENTS (M/F, 15/16)

**SCENE 2: ቅዱስ , ብሩክ AND አቶ ደንበል CROSS THE BORDER TO KISIMBA**

- አቶ ደንበል (M, 40)
- ቅዱስ (M, 8)
- ብሩክ (M, 8)
- THUG 1 (M, ?)

**SCENE 3: ምህረት TALKS TO PRINCIPAL ርዕሰ መምህርት ሰብለ AFTER CLASS**

- ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)
- ምህረት (F, 15)

**SCENE 4: ምህረት VISITS ትዕግስት IN BED**

- ምህረት **(F, 15)**
- ትዕግስት **(F, 15)**

## 1. INTRO:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉ ተከታታይ ድራማ ነዉ። እስቲ ያለፈውን መለስ ብለን እናስታውስ።

የምህረት መንትያ ወንድሞች በስተመጨረሻ ወደቤታቸው በጉዞ ላይ ናቸው። ለነገሩማ አክስታቸው ወ/ሮ ለምለም እንዲያሳድጓቸው ነበር። ነገር ግን አክስትየው በአንድ የማዕድን ማውጫ እንዲሰሩ ነው የላኳቸው። ልጆቹም ከዛ ለማምለጥ ተሳክቶላቸውም አንድ ቀና ሰው መንገድ ላይ አግኝቷቸው ሊረዳቸው በመኪናው አሳፍረዋቸዋል:

2. አቶ ደንበል **(EP 20, LINE 55):** "በዚህ መኪና በፍጥነት ልንዳ አልችልም። ዕድለኞች ከሆንን ነገ እንደርሳለን።" **(+57)** "በነገራችን ላይ ማንም ሰው ቢጠይቃችሁ አባታችን ነው ነው የምትሉት።

3. ብሩክ **&** ቅዱስ **(62):** "እሺ."

ብሩክ እና ቅዱስ ከቤተሰቦቻቸው ጋ መቀላቀል ይችሉ ይሆን? አስታውሱ ወላጆቻቸው የት እንዳሉ እንኳን አያውቁም። - ወላጆቻቸው በቅርቡ አዲስ ቤት ቀይረዋል። ... በዛ ላይ አባትየው አቶ ሙላቱ ከፖሊስ ሸሽተው የባለቤታቸው ወላጆች ዘንድ ለመደበቅ ገጠር ሄደዋል። የልጆቹ እህት ምህረትስ ? ከፍቅረኛዋ ዳንኤል ጋ የምታደርገው መለው ጠፍቷታል። ለመጀመሪያ ጊዜ ከሱ ጋ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅማለች። በማግስቱ ጠዋት ከእንቅልፏ ስትነቃም በሰራችው ስራ ፀፀት ተሰምቷታል። : **(KW BEGIN)**

4. ምህረት **(EP 20, LINE 11/13):** "ኦ የኔ ነገር ምን ጉድ ነው የሰራሁት? (...)ከአሁን በኋላ ጨዋልጅ አይደለሁም።! (...)... ጥፋተኝነት ... እና ሀፍተት ነው የሚሰማኝ።.." **(KW END)**

ምህረት ጥፋተኛነቷን ትቋቋመው ይሆን? በዳንኤልስ ላይ ዕምነት ይኖራታል? እሱስ ምን አይነት ርምጃ

ይወስድ ይሆን? ባለፈው ክፍል ከአባቱ ጋ እራት እየበሉ ያደረጉት ውይይት ሰኪታማ አልነበረም።:

5. ዳንኤል (EP 22, 58): "አባዬ አታዳምጠኝም ልበል። ምንም ይሁን ምን ያንተ ድርጅት ጨርሶ አያሳስበኝም።"

6. KANYAMA: "ዳንኤል፤ የቤተሰቡን ድርጅት ከመቀላቀል አሻፈረኝ ልትል ትችላለህ። ነገር ግን የውጭ ሀገር ሰው ቤተሰቤን እንዲቀላቀል አልፈልግም። እዚህ ካለቺው ልጅ ጋ ያለህን ግንኙነት አቁመህ አብረኸኝ ወደቤታችን እንድትመጣ ነው የምመክርህ።"

ዳንኤል አባቱን ተከትሎ ወደ ላቦሪያ ይሄድ ይሆን? መልሱን ከዛሬው « ጥሩ እና መጥፎ ዜና ከሚለው የጭውውቱ 23ኛ ክፍል እንጠብቅ። ፖሊሶች የምህረትን አባት አቶ ሙላቱን ለማሰር ቤታቸው ሄደው እቃቸውን ምስቅልቅሉን ቢያወጡትም ምህረት በማግስቱ ጠዋት በትምህርት ገበታዋ ላይ ተገኝታለች።

**<u>SCENE 1: ምህረት IN SCHOOL</u>**

**7. SFX: CLASSROOM ATMO**

**8. SFX: ዳንኤል 'S FOOTSTEPS APPROACHING**

**9. ዳንኤል :** ታድያስ ምህረት። ምንድን ነው ዛሬ የደከመሽ ትመስያለሽ…

**10. ምህረት :** ደህና ነኝ ዳንኤል ።

**11. ዳንኤል :** እሺ (hesitating) ምህረት ልረብሽሽ አልፈልግም ግን-

**KW BEGIN**

**12. ምህረት :** አሁን አይመቸኝም ዳንኤል። ክፍል ውስጥ ነን እሺ? በኋላ እናውራ።

**13. ዳንኤል :** (concerned) ግን ማውራት አለብን በጣም አስፈላጊ ነው።

**14. ምህረት :** (firmly) ዳንኤል ስለእሱ ማሰብም ይሁን ማውራት አሁን አልፈልግም እሺ።

15. ዳንኤል : እንዴ ምን መሰሎሽ ነው … ስለእኔ --

KW END

16. SFX: DOOR OPENING

17. SFX: HIGH-HEELED FOOTSTEPS APPROACHING

18. ርዕሰ መምህርት ሰብለ: (orders) ዳንኤል ወደ መቀመጫህ ተመለስ ምህረትን አትረብሽ !

19. ዳንኤል : እሺ ርዕሰ መምህርት

20. ርዕሰ መምህርት ሰብለ : መልካም ። በባዮሎጂ ፈተና ከፍተኛውን ውጤት ያመጣውን ከመናገሬ በፊት አንድ ማስታወቂያ አለኝ።

21. SFX: GRUMBLES FROM STUDENTS

22. ርዕሰ መምህርት ሰብለ : (plainly) ምናልባት ሰምታችሁ ይሆናል። …ከሚቀጥለው ሴሚስተር በኋላ ዳንኤል ካሳሁን የኛ ተማሪ አይሆንም። ወደ ላቦሪያ ይመለሳል። እና በርግጥ በመሄዱ እናዝናለን።

23. SFX: SHOCKED MURMURS FROM STUDENTS

24. ምህረት : (totally shocked) ምን?

25. ንጉሴ : (trying to suppress laughter)

26. SFX: LOW MURMURS FROM STUDENTS

27. ርዕሰ መምህርት ሰብለ : ፀጥታ ሁላችሁም።

SILENCE

28. JULETTE: ጥሩ። አሁን ውጤታችሁን ልስጣችሁ። በዚህ ፈተና ከፍተኛውን ነጥብ ያገኘው … (announces) ንጉሴ ጃለታ ነው!

**29. SFX: CLAPS AND APPLAUSE FROM STUDENTS** “ንጉሴ!” “ንጉሴ !”

**30.** ንጉሴ : **(proudly)** አመሰግናለሁ ርዕሰ መምህርት።

**31.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ : ምስጋና አይገባም ንጉሴ - አንተ ነህ ፈተናውን በከፍተና ነጥብ ያለፍከው። ሁለተኛ ምህረት ሙላቱ። የተቀራችሁትም ጥሩ ውጤት ነው። ሆኖም ስለ ዘገምታዊ ለውጥ ወይንም እድገት እንደገና ምዕራፉን ብትከልሱት ጥሩ ነው። በተለይ ደግሞ ትዕግስት ። ከሁሉም ጥሩ ያልሆነ ነጥብ ነው ያገኘችው።

**32. SFX: STUDENTS LAUGHING UNCONTROLLABLY**

**33.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ : ፀጥታ። አሁን ትስቁባታላችሁ ጠንክራቹህ ካልሰራችሁ በሚቀጥለው ጊዜ ራሳቹሁ ይሆናል የሚሳቅባችሁ ። ምህረት ትዕግስት ለምን እንዳልመጣች የምታውቂው ነገር አለ?

**34.** ምህረት : ታማለች። ጥሩ ስሜት እንደማይሰማት ነግራኝ ነበር።

**35.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ : መልካም ። ጓደኛዋ ስለሆንሽ የትምህርትክፍለ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ ልትወስጂላት ትችያለች። እእ እ ምህረት – በኋላ ለአንድ አፍታ ቢሮዬ እንድትመጪ። አንዳንድ በፈተና ላይ ስለነበሩት ጥያቄዎች የምነግርሽ አለኝ። ...**SFX: PAPER RUSTLE**

**36. MUSIC INTERLUDE**

<u>**SCENE 2:** ቅዱስ , ብሩክ **AND** አቶ ደንበል **CROSS THE BORDER TO KISIMBA**</u>

**37. SFX: TRUCK DRIVING ON A ROUGH ROAD, RADIO ON**

**38.** አቶ ደንበል : ልጆች አሁን ወደ ሀገራችን ድንበር እየተዳረስን ነው። ለፍተሻ የድንበሩ ጠባቂዎች ለተወሰነ ጊዜ ስለሚያቆሙን ከሁለት አንዳችሁ ሽንቱን መሽናት የሚፈልግ አለ?

39. ቅዱስ : (screams joyfully) እኔ!

40. ብሩክ : (calmly) እኔም መሄድ እፈልጋለሁ።

41. አቶ ደንበል : ጥሩ እንግዲያውስ የምቆምበት ቦታ ልምረጥ።

42. SFX: TRUCK SLOWLY COMING TO A HALT

43. አቶ ደንበል : ይኼው - በሉ ፍጠኑ። ልጆች ብዙ ርቃችሁ እንዳትሄዱ። እኔ እዚሁ እጠብቃችኋለሁ።

44. SFX: TRUCK DOOR OPENING

45. ATMO COUNTRYSIDE INSECTS

46. SFX: FOOTSTEPS OF THE TWO BOYS LEAVING, ON GRASS (WE FOLLOW THEM)

47. ብሩክ : ቅዱስ ማንም መንገዱ ላይ እንዳያየን ና ከዚህ ዛፍ ጀርባ እንሸሸግ።

48. አቶ ደንበል : (far away) ፍጠኑ ልጆች ጀንበር ከመጥለቋ በፊት እንድንደርስ።

49. SFX: PEEING SOUND ON THE GROUND

50. FAR AWAY: SFX: STONE THROWN AND WINDOW BROKEN

51. FAR AWAY: SFX: RAPID FOOTSTEPS APPROACHING

52. THUG 1: ስማ ሹፌር ከመኪናው ውስጥ ውረድና የኋላውን በር ክፈት።

53. አቶ ደንበል: (scared stiff) እሺ ያልከኝን በሙሉ አደርጋለሁ።ብቻ እንዳትተኩስ – እባክህን እንዳትተኩስብኝ…

54. SFX: PEEING SOUND ON THE GROUND STOPS (SIMULTANEOUSLY)

55. ቅዱስ : ብሩክ ይሰማሀል? ድምፁ የመጣው ከመኪናው ነው?

**56.** ብሩክ **:** አዎን እኔም ሰምቻለሁ። እስኪ ምን እንደሆነ ላጣራ።

**57. SFX: ZIPPER CLOSED, CLOTHING RUSTLING**

**58. SFX: FOOTSTEPS WALKING CAREFULLY ON GRASS, THEN RUNNING BACK**

**59.** ብሩክ**:** **(whispers in fear)** ቅዱስ ቶሎበል እንደበቅ። የሆኑ ሰዎች ከ አቶ ደንበል መኪና ከረጢቶች እየሰረቁ ነው!

**60.** ቅዱስ **:** **(starts to cry)**

**61.** ብሩክ**:** **(whispering)** እሽሽ! ዝም በል ቅዱስ። ወደ መሬት ለጥ በል። ብቻ አቶ ደንበልን ባልገደሏቸው !

**PAUSE - JUST COUNTRYSIDE ATMO**

**KW BEGIN**

**62.** ቅዱስ : አሁንም እዚያ ናቸው?

**63.** ብሩክ : አዎን! ብዙ ከረጢቶች ወስደው ወደ፣ ወደ ጫካው እየገቡ ነው።

**64.** ቅዱስ : በጣም ነው የፈራሁት። እኔ መሮጤ ነው!

**65.** ብሩክ : ቆይ ቅዱስ ተመልሰው አለመምጣታቸውን እስክናረጋግጥ እዚህ ፀጥ ብለን መቆየት አለብን።

**KW END**

**PAUSE - JUST COUNTRYSIDE ATMO**

**66. SFX: FOOTSTEPS APPROACHING RAPIDLY THROUGH HIGH GRASS**

**67.** ቅዱስ **:** መጡብን!

**68. ቅዱስ AND ብሩክ BREATHING HARD IN FEAR**

**69. አቶ ደንበል:** **(screaming in panic)** ልጆች?

**70. ብሩክ:** **(to** ቅዱስ **)** እነሱ አይደሉም አቶ ደንበል ናቸው ! **(shouting to** አቶ ደንበል **)** እዚጋ ነን!

**71. አቶ ደንበል** : ልጆች! እዚህ ጋ ናችሁ። ደህና ናችሁ?

**72. ብሩክ** : አዎን የሆነውን ተመልክተናል። ግን ወደ ዕርሶ ለመምጣት ስለፈራን ነው።!

**73. አቶ ደንበል** : ጥሩ ነው ያደረጋችሁት። ደግነቱ ሌላ መኪና መምጣቱን ሲመለከቱ ጊዜ ሸሹ። … ግን ቶሎ ብለን ከዚህ ቦታ መሸሽ አለብን። ሌሎች ዘራፊዎች ሳይመጡ። እንሂድ ልጆች።!

**74. MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: ምህረት TALKS TO PRINCIPAL ርዕሰ መምህርት ሰብለ AFTER LESSON</u>**

**75. OFFICE ATMO**

**76. SFX: DOOR CLOSED BEHIND THEM**

**77.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ : ምህረት እንኳን መጣሽ። ተቀመጭ። ብዙ ጊዜ አይፈጅም። እንድትመጪ የፈለኩበት ምክንያት በውጤትሽ ስላልተደሰትኩ ነው።

**78.** ምህረት**:** **(confused)** ግን… መምህርት ከክፍል እኮ ሁለተኛ ነበርኩ።

**79.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ **:** ትክክል። ለምን ሁለተኛ ወጣሽ?

**80.** ምህረት **:** የተቻለኝን ያህል አድርጌያለሁ መምህርት። - እመኑኝ በደንብ ነው ያጠናሁት።

**81.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ **:** ግን ከዚህ የበለጠ መስራት ትችይ ነበር ብዬ አስባለሁ። በተለይ ከአንድ ሰው ጋ ብዙ ሰዓት ማባከን ስለጀመርሽ ይመስለኛል።

**82.** ምህረት **:** ምን ማለትዎ ነው መምህርት?

**83.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ **:** ከዳንኤል ካሳሁን ጋ ብዙ ጊዜሽን በማውራት ማሳለፍ እንደምትወጂ ተመልክቼያለሁ።

**84.** ምህረት **:** ግን … እርሶ እንደሚያስቡት አይደለም እኔ --

**KW BEGIN**

**85.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ **: (firmly)** አልጨረስኩም ምህረት። በርግጥ በጣም ቆንጆ ልጅ ነሽ በዛ ላይ ብልህ። ግን አላማሽን እንዳትረሺ። እዚህ ት/ቤት እንድትገቢ እድሉን የሰጠሁሽ በችሎታሽ ስለተማመንኩ ነው። ብዙ ተማሪዎች ይህንን ነፃ የትምህርት እድል ለማግኘት ያልማሉ። እና በቸልተኝነት አትይው። ስለዚህ ይህ እንደሚገባሽ በየቀኑ እንድታረጋግጭልኝ እፈልጋለሁ።

**86.** ምህረት**:** **(feeling guilty)** አውቃለሁ… ትንሽ…እቤት …ቤተሰቦቼ ዘንድ ችግር ስላለ። ለዛ ነው የትኩረቴ እቅጣጫ የተዛባው።

**87.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ **:** ቤተሰብ? አባትሽ አሁንም ያንቺን በቦንጎ አካዴሚ መማር ይቃወማል? እኔ ደግሞ ችግሩን የፈታነው መስሎኝ ነበር።

**88.** ምህረት **:** የለም የለም። እንደዛ አይደለም። በእውነት መምህርት በሚቀጥለው ጊዜ ይበልጥ ጠንክሬ እንደምሰራ ቃል እገባልዎታለሁ።

**KW END**

**89.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ **:** ምህረት አላማሽን ግቡን እስኪመታ ምንም ነገር ትኩረትሽን አያስተጓጉለው። ባንቺ ላይ ትልቅ ተስፋ ነው የጣልኩት። እኔ ከምን ተነስቼ የት እንደደረስኩ ብቻ አይደለም የምታስታውሺኝ። የብዙ ልጃገረዶች ህልም ዕውን መሆኑንም የምትወክይ ታታሪ ልጅ ነሽ። እንዳታዋርጂን አደራ። በይ አሁን ሂጂ።

**90.** ምህረት : ግድየለም። የተቻለኝን ሁሉ አድርጌ እርሶዎ በእኔ እንዲኮሩ አደርጋለሁ።

**91.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ **: (pleased)** ምህረት ይህንን ነበር መስማት የፈለኩት። አሁን ወደ ክፍልሽ ልትመለሽ ትችያለሽ።

**92. SFX CHAIR BEING PUSHED BACK**

**93. MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 4:</u>** <u>ምህረት</u> **<u>VISITS</u>** <u>ትዕግስት</u> **<u>IN BED</u>**

**94. SFX: GENTLE KNOCK ON DOOR**

**95.** ትዕግስት**:** **(from inside)** ይግቡ…

**96. SFX: DOOR BEING OPENED WIDE**

**97.** ምህረት : ታድያስ ትዕግስት! ሰራተኛዋ ግቢ ብላኝ ነው።

**98.** ትዕግስት**:** ታድያስ፤ እንኳን መጣሽ።

**99.** ምህረት **:** **(amazed)** ይህ ያንቺ መኝታ ቤት ነው? ፐ! እንዴት ያምራል።… ትዕግስት ሳልረሳው የባዮሎጂ ፈተናሽን ይዤልሽ መጥቻለሁ።

**100.** ትዕግስት**:** **(anticipating bad news)** ኦ እሺ…

**101. SFX: PAPER BEING HANDLED…THEN RIPPED UP**

**102.** ምህረት : ትዕግስት፤ ምን እያደረግሽ ነው? የፈተና ወረቀትሽ እኮ ነው። ውጤትሽን ለወላጆችሽ አታሳይም?

**103.** ትዕግስት: ለእነሱ ማሳየት? እዚህ ወረቀቴን የማሳየው ሰው ይታይሻል? ወላጆቼ እዚህ የሉም። በስንት አንዴ ነው የማገኛቸው።... ለማንኛውም ምን አዲስ ነገር አለ?

**KW BEGIN**

**104.** ምህረት : ውይ ትዕግስት... ከየት እንደምጀምርልሽ አላውቅም። ሰሞኑን ብዙ ነገሮች ነው የተከሰቱት። ... እራሴን የሳትኩ ያህል ነው የሚሰማኝ።

**105.** ትዕግስት: እረ ባክሽን! ጭንቅላትሽን ለሚቀጥለው ፈተና ለሁላታችንም እንዲያስብ እፈልገዋለሁ።

**106. (They both laugh)**

**KW END**

**107.** ምህረት : በመጀመሪያ ነገር ዳንኤል ወደ ላቦሪያ መመለሱ ነው!

**108.** ትዕግስት: ምን? እስከናካቴው?

**109.** ምህረት : አዎ! ርዕሰ መምህርት ሰብለ ናቸው የነገሩን። ከዛ ቀደም ብሎ ላናግርሽ ሲለኝ እኔ ደግሞ ለሌላ ነገር መስሎኝ አሁን አልችልም አልኩት። ከዚህ ለቆ እንደሚሄድ ሊነግረኝ እንደነበር አላወኩም ነበር።!

**110.** ትዕግስት: አንቺስ ምን ትሆኛለሽ?

**111.** ምህረት : አላውቅም ትዕግስት። ይኼ እኮ ነው የሚያስፈራኝ። ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ብዙ የሚያስጨንቁኝ ነገሮች አሉ። ንጉሴ በጣም ለኔ ጥሩ ነበር። እና... አላውቅም። እንደውም ከገመትኩት በላይ ስለሱ ማሰላሰል ጀምሬያለሁ። ወይኔ ትዕግስት! ከኔ ብዙ የሚጠብቁ በርካታ ሰዎች አሉ።

**112.** ትዕግስት**:** ቆይኝ ቆይኝ። ንጉሴ ነው ያልሽው? ምህረት - ከ ንጉሴም ፎንቃ ያዘሽ እንዴ?

**113.** ምህረት : ትዕግስት በአሁኑ ሰዓት ምንም የማውቀው ነገር የለም። ይኼ ፍቅረኛ የሚሉት ጉዳይ ናላዬን እየበጠበጠው ነው። በዛ ላይ መምህራችን ለምን በፈተና ከክፍል አንደኛ እንዳልወጣሁ ጠይቀውኛል። በኔ ላይ ምን ያህል ተስፋ እንደጣሉ ነገሩኝ።

**114.** ትዕግስት**:** **(sarcastic)** በይ እንኳን ደስ ያለሽ። እዚህ የመጣሽው ምን ያህል ጎበዝ እንደሆንሽ ልትነግሪኝ ነው?

**115.** ምህረት : አይደለም... አንድ ነገር ልጠይቅሽ ነው። የወር አበባ መቀበያ ካለሽ እንድታውሺኝ ነው። በቅርቡ ፔሬድ ይመጣል።

**116.** ትዕግስት**:** **(anxious)** ግን – ምህረት በዚህ ወር የወር አበባሽ መጥቶ ነበር አይደል?

**117.** ምህረት **:** አልመጣም... እሱን እኮ ነው የምልሽ – ዘግይቷል።

**118.** ትዕግስት: ወይ ጉድ!

**119. MUSIC INTERLUDE**

## 120. OUTRO/ MODERATOR:

ይህ አሳሳቢ ወሬ «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» በሚል ርዕስ የሚቀርበውን የበማድመጥ መማር ድራማ 23ኛ ክፍል ወደ መቋጫው ያደርስልናል። ትልቁ ጥያቄ ምህረት እርግዛ ይሆን የሚለው ነው? መልሱን በሚቀጥለው ክፍል እንደርስበታለን። ይህንን ክፍል ደግመው መስማት ከፈለጉ dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ- ገፃችንን ይጎብኙ፤ አልያም በፌስቡክ አድራሻችን ላይ ይከታተሉ። እስከሚቀጥለዉ ጊዜ ጤና ይስጥልን።